# የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች አምራች፣ አስመጪ እና ላኪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር

## ረቂቅ መመሪያ ቁጥር …/2017

ረቂ

መጋቢት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ይዘት ገጽ

መግቢያ ........ 1

ክፍል አንድ ........ 1

ጠቅላላ ........ 1

1) አጭር ርዕስ ........ 1

2) ትርጓሜ ........ 1

3) የተፈፃሚነት ወሰን ........ 4

**ክፍል ሁለት** ........ 4

**ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት** ........ 4

4) የግብርና መሳሪያ ለማምረት፣ መገጣጠም፣ ማስመጣትና መላክ ስራ ለመሰማራት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ........ 4

5) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት ........ 4

6) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማይጠየቅባቸው ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ........ 5

7) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት ........ 5

8) የአድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ ........ 6

9) ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለመስጠት ........ 6

10) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ ........ 6

ክፍል ሶስት ........ 6

የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ........ 6

11) ከፍተኛ የግብርና መሳሪያ አምራች ወይም ገጣጣሚ ሰው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች . 7

12) መካከለኛ የግብርና መሳሪያ አምራች ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ........ 7

13) አነስተኛ የግብርና መሳሪያ አምራች ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ........ 8

14) ከፍተኛ የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ........ 8

15) መካከለኛ የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ........ 9

16) አነስተኛ የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ........ 10

ክፍል አራት ........ 10

ስለ ግብርና ሜካናይዜሽን ባለሙያና ቴክኒሽያን ........ 10

17) የባለሙያና ቴክኒሽያን ብዛትና ስብጥር ........ 10

18) የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ........ 11

ክፍል አምስት ........ 13

ስለግብርና መሳሪያ ገላጭ ጽሁፍ......13
19) የግብርና መሳሪያ ገላጭ ጽሁፍ ይዘት......13
ክፍል ስድስት......14
ስለግብርና መሳሪያ ድህረ-ሽያጭ አገልግሎቶች......14
20) ስለድህረ-ሽያጭ አገልግሎት አይነቶችና መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች......14
ክፍል ሰባት......15
ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት እና ወደ ውጭ ስለመላክ......15
21) የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት......15
22) በልዩ ሁኔታ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገባ የግብርና መሳሪያ......15
23) የግብርና መሳሪያ ወደ ውጭ ስለመላክ......16
ክፍል ስምንት......16
ስለቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ......16
24) የቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታ......16
25) የቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች......16
ክፍል ዘጠኝ......19
ከጉምሩክ በር መልቀቂያ ፈቃድ ስለመስጠት......19
26) ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ የግብርና መሳሪያ ከጉምሩክ በር የመልቀቂያ ፈቃድ ስለመስጠት 20
27) ወደ ውጪ ሀገር ለሚወጣ የግብርና መሳሪያ የጉምሩክ የይለቀቅ ፈቃድ ስለመስጠት......20
28) የግብርና መሳሪያ ከጉምሩክ በር ወደ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ ስለሚከለከልበት ሁኔታ......21
**ክፍል አስር**......21
**ስለ ኢንስፔክተሮች**......21
29) የኢንስፔክተሮች ሥልጣንና ተግባር......21
ክፍል አስራ አንድ......22
አስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ......22
30) ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት......22
31) ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ......23
32) ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ......23
33) የግብርና መሳሪያ ስለመያዝ......24
34) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ......24
35) ስለ ቅሬታ አቀራረብ......24

ክፍል አስራ አንድ ........ 24
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 24
36) መረጃ ስለመያዝ ........ 24
37) መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ ........ 24
38) የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ........ 25
39) መመሪያውን ስለ ማሻሻል ........ 25
40) የመተባበር ግዴታ ........ 25
41) ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች ........ 25
42) መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ........ 25
ዕዝሎች ........ 26

## መግቢያ

የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች በማስመጣት፣ በማምረት፣ በመገጣጠም እና በመላክ ንግድ ስራ ላይ የሚሰማራ ድርጅት ግልጽ የምዝገባና ቁጥጥር አሰራር ስርዓት በመዘርጋት መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በመስጠት የጥራት ደረጃው፣ ደህንነቱ ወይም ውጤታማነቱ የተረጋገጠ የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያ እንዲሁም የድሕረ-ሽያጭ አገልግሎትን እንዲያቀርብ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ተፈላጊ መስፈርቶችንና የግብርና ስታንዳርድን በማሟላት ጥራቱ፣ ደህንነቱና ውጤታማነቱ የተረጋገጠ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር እንዲገባ የቁጥጥር አሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ግልፅነት፣ ተደራሽነትና ተጠያቂነትን ያለው አሰራር በመዘርጋት ከግብርናው ዘርፍ የሚገኘውን ጠቀሜታ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ለግብርና ሚኒስቴር ተለይቶ በተሰጠው አንቀጽ 20 በንዑስ አንቀጽ 1/ (ሸ) እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 509/2011 ዓ.ም ላይ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የግብርና ሚኒስቴር ይህን "የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች አምራች፣ አስመጪ እና ላኪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1) አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የግብርና መሳሪያዎች አምራች፣ አስመጪ እና ላኪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር** .../2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2) ትርጓሜ

በደንብ ቁጥር 509/2014 አንቀፅ 2 ሥር ለተመለከቱ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ነው፡፡
2. "ደንብ" ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን አደረጃጀት ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 509/2014 ነው፡፡
3. "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤
4. "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ነው፡፡

5. “የግብርና ሜካናይዜሽን” ማለት በሰው ሀይል፣ በእንስሳት፣ ወይም በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀሱ፣ የግብርና ስራዎችን ውጤታማነት የሚያሳድጉ፣ የሰው ጉልበትን የሚቀንሱ፣ ጊዜን የሚቆጥቡ መሳሪያዎችን እና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ሂደት ነው፤
6. “የግብርና መሳሪያ” ማለት በግብርና ምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የግብርና ማሽን ወይም የግብርና መገልገያ ዕቃን የሚያካትት ነው፤
7. “የግብርና ማሽን” ማለት በነዳጅ፣ በኤሌክትሪክ፣ ወይም በታዳሽ የሀይል ምንጭ የሚንቀሳቀስ ለግብርና ስራ አገልግሎት የሚውል ማለትም ትራክተር፣ ማጨጃ፣ አጭዶ መውቂያ፣ መውቂያ፣ መፈልፈያ፣ ኬሚካል መርጫ፣ ለመስኖ ልማት የሚውሉ ፓምፕ፣ ለወተት፣ ለዓሣ፣ ለዶሮ፣ ለንብና ለሐር እንዲሁም ለእንስሳት ልማት የሚውሉትንም ሆነ የግብርና ምርቶችን ለማዘጋጃ፣ ማጓጓዣና ማቀነባበር ስራ የሚያስፈልጉትን፣ ለእንሰሳት መኖ ዝግጅት፣ ለአፈርና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት የሚያገለግሉትን እና ሌሎች ተመሳሳይ ማሽኖችን  የሚያካትት ነው፤
8. “የግብርና መገልገያ” ማለት በግብርና ማሽን ወይም በእንስሳት ላይ የሚገጠም ወይም በሰው ጉልበት የሚሰራ የግብርና ስራን ለማከናወን የሚያገለግል ዕቃ ነው፤
9. “ሞተር” ማለት የተለያዩ የኃይል አይነቶችን (በኤሌክትሪክ፣ ነዳጅ ወይም በታዳሽ ሀይል) በመጠቀም ወደ ሜካኒካል ኃይል እና እንቅስቃሴ የሚለውጥ ነው።
10. “በሞተር የሚሰሩና ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ” ማለት ትራክተርና አጭዶ መውቂያን ጨምሮ በውስጣቸው በተገጠመ ሞተር ወይም በውጪ አብሮ በተገጠመ አንቀሳቃሽ ሞተር በመሽከርከር የግብርና አገልግሎትን የሚሰሩ ማሽኖችን የያዘ ነው።
11. “በሞተር የሚሰሩና ከቦታ ቦታ በራሳቸው ሀይል የማይንቀሳቀሱ” ማለት በውስጣቸው በተገጠመ ወይም በውጪ አብሮ በተገጠመ አንቀሳቃሽ ሞተር በውስን ቦታ ለተለያየ የግብርና አገልግሎት የሚውሉ ማሽኖች  የያዘ ነው።
12. “በሰው ኃይል ወይም በእንስሳት የሚሰሩ” ሞተር የማይጠቀሙ በሰው ወይም በእንስሳት ጉልበት በመታገዝ የግብርና አገልግሎትን ለማከናወን የሚውሉ መሳሪያዎች ናቸው።
13. “ተቀጽላ መሳሪያዎች” ማለት በትራክተር፣ በእንሰሳት ወይም በሰው ጉልበት የሚጎተቱ የተለያዩ የግብርና ስራዎችን ለማከናወን የሚውሉ የግብርና መገልገያ መሳሪያዎች ናቸው።
14. “የድህረ ሽያጭ አገልግሎት” ማለት አምራቹ ወይም አስመጪው ከመሳሪያ ሽያጭ በኋላ ለገዢው የሚያቀርበው የስልጠናና ምክር አገልግሎት፣ የመለዋወጫ ዕቃ፣ የዋስትና እና የጥገና አገልግሎት ማለት ነው።
15. “ወርክሾፕ” ማለት የግብርና መሳሪያ ጥገና ወይም ሌሎች የማስተካከያ ስራዎች የሚከናወንበት መሰረታዊ ቁሳቁሶችና መሳሪያ የተሟሉበት ቦታ ነው፤
16. “ተንቀሳቃሽ ጋራዥ” ማለት ለግብርና መሳሪያዎች የጥገና ስራ የሚያገለግሉ የተለያዩ የጥገና መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን የያዘ ልዩ ተሽከርካሪ ነው።
17. “ቴክኒሽያን” ማለት የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያ ላይ ለመስራት የሚያበቃ ስልጠና፣ አግባብ ያለው የሥራ ልምድ እና የሙያ ብቃቱ በምዘና የተረጋገጠ ሰው ነው።
18. “ባለሙያ” ማለት በግብርና ምህንድስና፣ በግብርና ሜካናይዜሽን ወይም በሌሎች ተዛማጅ የትምህርት መስኮች ዲግሪና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያለው ሰው ነው።
19. “አስተዳደራዊ እርምጃ” ማለት በባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑን በሚወክል አካል የሚወሰድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ የብቃት ማረጋገጫ ዕገዳ ወይም ስረዛ እርምጃዎች ናቸው።
20. “የመሳሪያ ጥራት” ማለት በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ወይም ወደ ሀገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ የግብርና መሳሪያዎች የግብርና ስታንዳርድና አስፈላጊ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን የሚገልጽ ነው።

21. "የመሳሪያ ደህንነት" ማለት በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ወይም ወደ ሀገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ የግብርና መሳሪያዎች በምርት፣ በክምችትና በማጓጓዝ ሂደት ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ወይም ከሚያውኩ ተፈላጊ ያልሆኑ የዕጽዋት ወይም የዕንስሳት ዝርያዎች ወይም ኬሚካሎች ነጻ መሆናቸውን እና የግብርና ስታንዳርድ ማሟላታቸውን የሚገልጽ ነው፡፡
22. "አዲስ መሳሪያ" ማለት ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በሌላ ሀገር ተመዝግቦ አገልግሎት ያልሰጠ ሆኖ ከተመረተ ሁለት ዓመት ያልበለጠው የግብርና መሳሪያ ነው፡፡
23. "ያገለገለ መሳሪያ" ማለት ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በሌላ ሀገር ተመዝግቦ ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ አገልግሎ ወደ ሀገር የገባ ወይም ከተመረተ ከሁለት ዓመት በላይ የሆነው የግብርና መሳሪያ ነው፡፡
24. "ልዩ ፈቃድ" ማለት የብቃት ማረጋገጫ ሳያስፈልግ የግብርና መሳሪያን ከንግድ ዓላማ ውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ፈቃድ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡
25. "ኤስ ኬ ዲ (ሰሚ ኖክድ ዳውን)" ማለት በከፊል ተበታትኖ ወይም ተፈታቶ ሳይገጣጠም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ የግብርና መሳሪያ ነው፡፡
26. "ሲ ኬ ዲ (ኮምፕሌት ኖክድ ዳውን)" ማለት ሙሉ ለሙሉ ተበታትኖ ወይም ተፈታቶ ሳይገጣጠም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ የግብርና መሳሪያ ነው፡፡
27. "ገጣጣሚ" ማለት በኤስ ኬ ዲ ወይም በሲ ኬ ዲ የሚቀርቡትን የግብርና መሣሪያ ክፍሎችን በመገጣጠም የሚያመርት ድርጅት ማለት ነው፡፡
28. "አምራች" ማለት ቢያንስ አንድ የግብርና መሣሪያ ማምረቻ ጥሬ ዕቃን አምርቶ እንዲሁም ከኤስ.ኬ.ዲ ወይም በሲ ኬ ዲ የሚቀርቡትን ግብዓቶችን ጨምሮ በመገጣጠም የግብርና መሣሪያ የሚያመርት ድርጅት ማለት ነው፡፡
29. "ከፍተኛ የግብርና መሳሪያ አምራች" ማለት በሞተር የሚሰሩና ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ፣ በሞተር የሚሰሩና ከቦታ ቦታ በራሳቸው ሀይል የማይንቀሳቀሱ፣ በሰው ኃይል ወይም በእንስሳት የሚሰሩ እንዲሁም ተቀጽላ መሳሪያዎች የሚያመርቱ ወይም የሚገጣጥሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡
30. "መካከለኛ የግብርና መሳሪያ አምራች" ማለት በሞተር የሚሰሩና ከቦታ ቦታ በራሳቸው ሀይል የማይንቀሳቀሱ፣ በሰው ኃይል ወይም በእንስሳት የሚሰሩ እንዲሁም ተቀጽላ መሳሪያዎች የሚያመርቱ ወይም የሚገጣጥሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡
31. "አነስተኛ የግብርና መሳሪያ አምራች" ማለት እስከ 20 የፈረስ ጉልበት ባለው ሞተር የሚሰሩና ከቦታ ቦታ በራሳቸው ሀይል የማይንቀሳቀሱ፣ በሰው ኃይል ወይም በእንስሳት የሚሰሩትን እንዲሁም ተቀጽላ መሳሪያዎችን የሚያመርቱ ወይም የሚገጣጠሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡
32. "አስመጪ" ማለት ማንኛውንም የግብርና ልማት ስራዎችን ለማከናወን የሚያገለግሉ መሳሪያዎችንና መለዋወጫዎችን ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ህጋዊ ፈቃድ ያለው ድርጅት ማለት ነው፡፡
33. "ከፍተኛ ግብርና መሳሪያዎች አስመጪ" ማለት በሞተር የሚሰሩና ከቦታ ቦታ በራሳቸው ሀይል የሚንቀሳቀሱትንም ሆነ የማይንቀሳቀሱትን፣ በሰው ኃይል ወይም በእንስሳት የሚሰሩትን እንዲሁም ተቀጽላ መሳሪያዎች የሚያስመጡ ወይም አስመጥተው የሚገጣጠሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡
34. "መካከለኛ የግብርና መሳሪያዎች አስመጪ" ማለት በሞተር የሚሰሩና ከቦታ ቦታ በራሳቸው ሀይል የማይንቀሳቀሱትን፣ በሰው ኃይል ወይም በእንስሳት የሚሰሩትን እና ተቀጽላ መሳሪያዎችን የሚያመርቱ ወይም የሚገጣጠሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡
35. "አነስተኛ የግብርና መሳሪያዎች አስመጪ" ማለት በሰው ኃይል ወይም በእንስሳት ብቻ የሚሰሩትን እንዲሁም ተቀጽላ መሳሪያዎች የሚያስመጡ ወይም አስመጥተው የሚገጣጠሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡
36. "የተመዘገበ የግብርና መሳሪያ" ማለት ተፈላጊ መስፈርቶችንና የግብርና ስታንዳርድን አሟልቶ በባለሥልጣኑ የተመዘገበ የግብርና መሳሪያ ነው፡፡

ረቂቅ

37. “የመልቀቂያ ፈቃድ” ማለት የግብርና መሳሪያ ከጉምሩክ በር ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በባለስልጣኑ የሚሰጥ የፈቃድ ሰነድ ነው፡፡
38. “የቅድመ የማስገቢያ ፈቃድ” ማለት የግብርና መሳሪያ ከወደብ ከመጫኑና ወደሀገራችን ከመግባቱ በፊት አስፈላጊ መስፈርቶችና የግብርና ስታንዳርድን ማሟላቱ ተረጋግጦ በባለስልጣኑ የሚሰጥ የዕውቅና ፈቃድ ነው፡፡
39. “ነጻ ናሙና” ማለት አንድ የግብርና መሳሪያ ለማስተዋወቅ ወይም ለምርምርና ጥናት ስራ የሚመጣ የግብርና መሳሪያ ነው፤
40. “መግቢያና መውጫ ኬላ ወይም የጉምሩክ በር” ማለት በጉምሩክ ኮሚሽን የተቋቋመ፣ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባበት ወይም ከሀገር የሚወጣበት የቁጥጥር ቦታ ነው፤
41. “ተቋም” ማለት የግብርና መሳሪያና መለዋወጫዎችን በማምረት፣ በመገጣጠም፣ በማስመጣት ወይም በመላክ ስራ ላይ የተሰማራ እና በባለስልጣኑ ደንብና በዚህ መመሪያ መሠረት ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግበት ድርጅት ነው፡፡

### 3) የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያ አስመጪ፣ ላኪ፣ ክልል ተሻጋሪ አምራች እና ገጣጣሚ ሰው እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ በሚገባና በሚወጣ የግብርና መሳሪያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

### 4) የግብርና መሳሪያ ለማምረት፣ መገጣጠም፣ ማስመጣትና መላክ ስራ ለመሰማራት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ

1. የግብርና መሳሪያዎችን ማምረት፣ መገጣጠም፣ ማስመጣት ወይም መላክ ስራ ላይ ለመሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የንግድ ስራ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና መሳሪያን ለንግድ የማምረት፣ የመገጣጠም፣ የማስመጣት ወይም የመላክ ስራ ላይ ለመሰማራት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

### 5) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ማንኛውም ሰው የግብርና መሳሪያዎችን ማምረት፣ መገጣጠም፣ ማስመጣት ወይም መላክ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል አስፈላጊ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-
   ሀ. በዚህ መመሪያ በክፍል ሶስት ስር ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ የጠየቀበትን መሠረታዊ መስፈርቶች ማሟላት፤
   ለ. በዚህ መመሪያ የተያያዘውን የመጠየቂያ ቅጽ (ዕዝል 1) በመሙላት በአካል ወይም በኢ-ሰርቪስ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤

ረቂቅ

ሐ. ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም

2. የአመልካቹ ቅድመ ሁኔታና ዝግጅት የተሟላ ከሆነ ድርጅቱ ከሁለት አባላት ያላነሰ በባለሥልጣኑ የሚመደብ የባለሙያ ቡድን እንዲታይ ይደረጋል፤
3. አመልካቹ አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ሲረጋገጥ እና ሲጸድቅ በባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ይደረጋል፤
4. በባለሙያ ቡድን ብቁነቱ ያልተረጋገጠ ድርጅት ሲያጋጥም ፈቃዱ የማይሰጥበት ምክንያት በጽሑፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፤
5. ድርጅቱ በጽሑፍ የተሰጠውን መስፈርት አስተካክሎ መገኘቱ ሲረጋገጥ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል እንደገና ታይቶና ተረጋግጦ የምስክር ወረቀቱ ሊሰጠው ይችላል፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው መሠረት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የበጀት አመቱ እስኪያልቅ ድረስ የጸና ይሆናል፤
7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንደአግባቡ በሕትመት ወይም በዲጂታል ዘዴ የተዘጋጀ ሊሆን ይችላል (ዕዝል 18)፡፡

## 6) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማይጠየቅባቸው ልዩ ልዩ ሁኔታዎች

ባለስልጣኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይስፈልግ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ልዩ የመልቀቂያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

1. ለሳይንሳዊ ምርምር እና ለትምህርት ተቋማት ለማስተማሪያ አገልግሎት የሚውል መሳሪያ ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ፤
2. ለአጭር ጊዜ ትምህርት፣ ስልጠና ወይም አውደ ርዕይ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ሲፈለግ፤
3. ለአስቸኳይ አደጋ፣ ለሰብልና እንስሳት ሕይወት አድን ተግባር ሲባል ወደ ሀገር ውስጥ መሳሪያ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ፤
4. በእርዳታ የመጣ ከሆነ፤
5. ለራስ ፍጆታ የሚውል መሳሪያ ከሆነ፤
6. ከላይ በዚህ አንቀጽ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተፈጠረው አጋጣሚ፣ ችግር ወይም ሁኔታ በማሳበብ የሚከናወን ሕገ-ወጥ ተግባር በማስረጃ ሲረጋገጥ በሕግ አግባብ አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

## 7) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት

ማንኛውም የግብርና መሳሪያዎችን አምራች፣ አስመጪ ወይም ላኪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊታደስለት የሚችለው፡-

1. በወቅቱ ይዞት የሚገኘው የምስክር ወረቀት ታግዶ ወይም ተሰርዞ ካልሆነ ወይም ድርጅቱ በራሱ ፈቃድ ሥራውን ካላቋረጠ፣
2. ባለሥልጣኑ ለዚህ ሥራ ዘርፍ ያወጣቸው መስፈርቶች የተጠበቁ ስለመሆናቸው በባለስልጣኑ ባለሙያዎች ዓመታዊ ክትትል ሲረጋገጥ፣
3. ድርጅቱ ለዕድሳት አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል እና በየዓመቱ ለዕድሳት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ (ከሐምሌ 1 እስከ ታሕሳስ 30 ባሉት ቀናት) ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣

4. በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ሳይታደስ የቀረ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት ሰጪው ሥራው መቀጠል ከፈለገ የተቀመጡትን መመዘኛዎች ስለማሟላታቸው በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ሲረጋገጥ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማውጣት ይችላል፡፡

## 8) የአድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

1. ማንኛውም የግብርና መሳሪያ አምራች፣ ገጣጣሚ፣ አስመጪ ወይም ላኪ ሰው ባለስልጣኑን ሳያሳውቅ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዛወር አይችልም፤
2. በማንኛውም የግብርና መሳሪያ አምራች፣ ገጣጣሚ፣ አስመጪ ወይም ላኪ ሰው የባለቤትነት ለውጥ ቢያደርግ ቀድሞ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለባለስልጣኑ መመለስ ይኖርበታል፤
3. ማንኛውም የግብርና መሳሪያ አምራች፣ ገጣጣሚ፣ አስመጪ ወይም ላኪ ድርጅት የባለስልጣን መ/ቤቱን ሳያሳውቅ ሌሎች መጋቢ ወይም ቅርንጫፍ ተቋማትን መክፈት አይችልም፡፡

## 9) ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለመስጠት

ቀደም ሲል የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ድርጅት ምትክ ሊያገኝ የሚችለው፡-

1. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ከሆነ ከነብልሽቱ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስና ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ፤
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ ስለመጥፋቱ የሚገልፅ ማረጋገጫ ከሚመለከተው አካል ሲያቀርብና ምትክ እንዲሰጠው ሲያመለክት፣
3. ለምትክ አሰጣጡ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል ብቻ ይሆናል፡፡

## 10) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ

ማንኛውም የግብርና መሳሪያ አምራች፣ ገጣጣሚ፣ አስመጪ ወይም ላኪ ድርጅት የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዋናውን ወይም ቅጅውን በንግድ ቤቱ ወይም በሽያጭ ክፍል ውስጥ በግልፅ በሚታይ ቦታ መስቀል ወይም ማስቀመጥ አለበት፡፡

# ክፍል ሶስት
# የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

## 11) ከፍተኛ የግብርና መሳሪያ አምራች ወይም ገጣጣሚ ሰው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

ማንኛውም ሰው በከፍተኛ የግብርና መሳሪያ አምራችነት ወይም ገጣጣሚነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶችን በዕዝል 2 ስር በተገለፀበት መልኩ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

1. አምራች ድርጅቱ ለመሳሪያ ማምረቻና የጥገና አገልግሎት መስጫ የሚሆን የስራ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤
2. የግብርና መሳሪያን ለማምረት ወይም ለመገጣጠም የሚያስችል ዎርክሾፕ እንዲሁም ድርጅቱ አምርቶ ለገበያ የቀረበ መሳሪያ የሚጠገንበት ወርክሾፕ ሊኖረው ይገባል፤
3. ወርክሾፑ የማምረቻ ወይም የመገጣጠሚያ ክፍሎችንና መሳሪያዎችን መያዝ አለበት፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና መሳሪያ ማምረቻ ወርክሾፕ ቢያንስ የመበየጃ ክፍል፣ የካስትና ሞልድ ክፍል፣ የምርምርና ስርጸት የስራ ክፍል፣ የተሟላ ማሽን ሾፕ (ሚሊንግ ማሽን፣ ፕላዝማ መቁረጫ፣ ሲኤንሲ ሌዝ ማሽን) ሊኖረው ይገባል፤
5. የጥሬ እቃ እና የመለዋወጫ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን መኖር አለበት፤
6. ተመርቶ ወይም ተገጣጥሞ ለተጠናቀቀና ለአገልግሎት ዝግጁ ለሆነ መሳሪያ ማቆያ የሚሆን መጠለያ መኖር አለበት፤
7. መሳሪያ ለማምረት ወይም ለመገጣጠም የሚያስፈልግ የሥራ ክፍል ባለሙያ እና ቴክኒሽያን ማሟላት አለበት፤
8. ድርጅቱ የሚያመርተውን ወይም የሚገጣጥመውን መሳሪያ አስመልክቶ ስልጠና ለመስጠት ቢያንስ 25 ሰው የሚይዝ የስልጠና ቦታና አስፈላጊ ግብዓት ሊኖረው ይገባል፤
9. ባለሙያና ቴክኒሺያንን ከአደጋ ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው አልባሳት፤ የእሳት አደጋ መከላከያ በወርክሾፕ፣ በመሳሪያ መጠለያ፣ በመጋዘን እንዲሁም ለእሳት አደጋ ተጋላጭ በሚባሉ ቦታዎች፣ በሁሉም የወርክ ሾፑ ክፍሎች የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መኖር አለበት፤
10. ለንጽህና መጠበቂያ በቂ ውሀ፣ ሻወር፣መታጠቢያና መጸዳጃ ለወንድና ለሴት ተለይቶ፤ ቁሳቁስ የተሟላለት ክፍል ወይም ቢሮ፣ የሰራተኛ መዝናኛ ክበብ፣ አመላካች የተጻፈበት ወይም የተለጠፈበት የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ፣የሰራተኛ የልብስ መቀየሪያና ማስቀመጫ ቦታ ለወንድና ለሴት ተለይቶ፣ የድንገተኛ አደጋ የማንቂያ ደውል፣ የአደጋ ጊዜ መውጫና መሰብሰቢያ ቦታ መሟላት አለበት፤
11. ማንኛውም ሰው በከፍተኛ የግብርና መሳሪያ ገጣጣሚነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለፀውን እንዲያሟላ አይገደደም፡፡

## 12) መካከለኛ የግብርና መሳሪያ አምራች ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

ማንኛውም ድርጅት በመካከለኛ የግብርና መሳሪያ አምራችነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶችን በዕዝል 3 ስር በተገለፀበት መልኩ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

1. አምራች ድርጅቱ ለመሳሪያ ማምረቻና የጥገና አገልግሎት መስጫ የሚሆን የስራ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤
2. የግብርና መሳሪያን ለማምረት የሚያስችል ዎርክሾፕ እንዲሁም ድርጅቱ አምርቶ ለገበያ የቀረበ መሳሪያ የሚጠገንበት ወርክሾፕ ሊኖረው ይገባል፤

3. ወርክሾፑ ቢያንስ የማምረቻ ክፍሎችንና ማምረቻ መሳሪያዎችን መያዝ አለበት፤
4. ተመርቶ ለተጠናቀቀና ለአገልግሎት ዝግጁ ለሆኑ መሳሪያ፣ የጥሬ እቃ እና የመለዋወጫ ማከማቻ መጋዘን መኖር አለበት መኖር አለበት፤
5. መሳሪያ ለማምረት የሚያስፈልግ የሚያስፈልጉ ለሥራ ክፍል ባለሙያ እና ቴክኒሽያን ማሟላት አለበት፤
6. የባለሙያና ቴክኒሺያንን ከአደጋ ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው አልባሳት፣ የእሳት አደጋ መከላከያ በወርክሾፕ፣ በመሳሪያ መጠለያ፣ በመጋዘን እንዲሁም ለእሳት አደጋ ተጋላጭ በሚባሉ ቦታዎች፣ የድንገተኛ አደጋ የማንቂያ ደውል፣ የአደጋ ጊዜ መውጫና መሰብሰቢያ ቦታ፣ በሁሉም የወርክ ሾፑ ክፍሎች የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መኖር አለበት፣
7. ለንጽህና መጠበቂያ በቂ ውሀ፣ ሻወር፣መታጠቢያና መጸዳጃ ለወንድና ለሴት ተለይቶ፣ ቁሳቁስ የተሟላለት ክፍል ወይም ቢሮ፣የሻይ ቡና አገልግሎት መስጫ ቦታ፤አመላካች የተጻፈበት ወይም የተለጠፈበት የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ፣የሰራተኞች የልብስ መቀየሪያና ማስቀመጫ ቦታ ለወንድና ለሴት ተለይቶ መኖር አለበት፣

## 13) አነስተኛ የግብርና መሳሪያ አምራች ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

ማንኛውም ድርጅት ለአነስተኛ የግብርና መሳሪያ አምራችነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶችን በዕዝል 4 ስር በተገለፀበት መልኩ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

1. አምራች ድርጅቱ ለመሳሪያ ማምረቻና የጥገና አገልግሎት መስጫ የሚሆን የስራ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤
2. የግብርና መሳሪያን ለማምረት የሚያስችል ዎርክሾፕ ሊኖረው ይገባል፤
3. ወርክሾፑ የማምረቻ መሳሪያን መያዝ አለበት፤
4. ተመርቶ ለተጠናቀቀና ለአገልግሎት ዝግጁ ለሆኑ መሳሪያ፣ የጥሬ እቃ እና የመለዋወጫ ማከማቻ መጋዘን መኖር አለበት፤
5. መሳሪያ ለማምረት የሚያስፈልግ ባለሙያ እና ቴክኒሽያን ማሟላት አለበት፤
6. የባለሙያና ቴክኒሺያንን ከአደጋ ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው አልባሳት፣ የእሳት አደጋ መከላከያ በወርክሾፕ፣ በመሳሪያ መጠለያ፣ በመጋዘን እንዲሁም ለእሳት አደጋ ተጋላጭ በሚባሉ ቦታዎች፣ የድንገተኛ አደጋ የማንቂያ ደውል፣ የአደጋ ጊዜ መውጫና መሰብሰቢያ ቦታ፣ በሁሉም የወርክ ሾፑ ክፍሎች የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መኖር አለበት፤
7. ለንጽህና መጠበቂያ በቂ ውሀ፣ ሻወር፣ መታጠቢያና መጸዳጃ ለወንድና ለሴት ተለይቶ፣ ቁሳቁስ የተሟላለት ክፍል ወይም ቢሮ፣ የሻይ ቡና አገልግሎት መስጫ ቦታ፤ አመላካች የተጻፈበት ወይም የተለጠፈበት የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ የሰራተኞች የልብስ መቀየሪያና ማስቀመጫ ቦታ ለወንድና ለሴት ተለይቶ መኖር አለበት።

## 14) ከፍተኛ የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

ማንኛውም ድርጅት በከፍተኛ ግብርና መሳሪያ አስመጪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶችን በዕዝል 5 ስር በተገለፀበት መልኩ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

1. አስመጪ ድርጅቱ ለመሳሪያ መጠለያ እና የጥገና አገልግሎት መስጫ የሚሆን የስራ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤
2. መሳሪያ ለመጠገን የሚያስችል ዎርክሾፕ ሊኖረው ይገባል፤
3. ወርክሾፑ የማምረቻ መሳሪያ ማሟላት አለበት፤
4. ለሚያስመጣው መሳሪያ በቂ የሆነ የመለዋወጫ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን መኖር አለበት፤
5. ለመሳሪያ ማቆያ የሚሆን በቂ መጠለያ ሊኖረው ይገባል፤
6. ላስመጣው መሳሪያ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልግ የሥራ ክፍል ባለሙያና ቴክኒሽያን ማሟላት አለበት፤
7. ድርጅቱ የሚያስመጣውን መሳሪያ አስመልክቶ ስልጠና ለመስጠት ቢያንስ 25 ሰው የሚይዝ የስልጠና ቦታና አስፈላጊ ግብዓት ሊኖረው ይገባል፤
8. የባለሙያና ቴክኒሺያንን ከአደጋ ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው አልባሳት፤ የእሳት አደጋ መከላከያ በወርክሾፕ፣ በመሳሪያ መጠለያ፣ በመጋዘን እንዲሁም ለእሳት አደጋ ተጋላጭ በሚባሉ ቦታዎች፣በሁሉም የወርክ ሾፑ ክፍሎች የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መኖር አለበት፤
9. የጽህፈት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል በቂ ቢሮና ቁሳቁስ፤ የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ፣ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ የሰራተኞች የልብስ መቀየሪያና ማስቀመጫ ቦታ እንዲሁም መታጠቢያና መጸዳጃ ለወንድና ለሴት ተለይቶ፣ የድንገተኛ አደጋ የማንቂያ ደውል፣ የአደጋ ጊዜ መውጫና መሰብሰቢያ ቦታ ማሟላት አለበት፡፡

## 15) መካከለኛ የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

ማንኛውም ድርጅት በመካከለኛ ግብርና መሳሪያ አስመጪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶችን በዕዝል 6 ስር በተገለፀበት መልኩ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

1. አስመጪ ድርጅቱ ለመሳሪያ መጠለያ እና የጥገና አገልግሎት መስጫ የሚሆን የስራ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤
2. የግብርና መሳሪያን ለመጠገን የሚያስችል ዎርክሾፕ ሊኖረው ይገባል፤
3. ወርክሾፑ ማምረቻ መሳሪያዎችን መያዝ አለበት፤
4. ለሚያስመጣቸው መሳሪያዎች በቂ የሆነ የመለዋወጫ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፤
5. ለመሳሪያ ማቆያ የሚሆን በቂ መጠለያ ሊኖረው ይገባል፤
6. ድርጅቱ ላስመጣቸው መሳሪያ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ የሥራ ክፍል ባለሙያና ቴክኒሽያን ማሟላት አለበት፤
7. የባለሙያና ቴክኒሺያንን ከአደጋ ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው አልባሳት፣ የእሳት አደጋ መከላከያ በወርክሾፕ፣ በመሳሪያ መጠለያ፣ በመጋዘን እንዲሁም ለእሳት አደጋ ተጋላጭ በሚባሉ ቦታዎች፣ የድንገተኛ አደጋ የማንቂያ ደውል፣ የአደጋ ጊዜ መውጫና መሰብሰቢያ ቦታ፣ በሁሉም የወርክ ሾፑ ክፍሎች የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መኖር አለበት፤

8. ለንጽህና መጠበቂያ በቂ ውሀ፣ ሻወር፣ መታጠቢያና መጸዳጃ ለወንድና ለሴት ተለይቶ፣ ቁሳቁስ የተሟላለት ክፍል ወይም ቢሮ፣ የሻይ ቡና አገልግሎት መስጫ ቦታ፤ አመላካች የተጻፈበት ወይም የተለጠፈበት የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ የሰራተኞች የልብስ መቀየሪያና ማስቀመጫ ቦታ ለወንድና ለሴት ተለይቶ መኖር አለበት፡፡

## 16) አነስተኛ የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

ማንኛውም ድርጅት ለአነስተኛ የግብርና መሳሪያ ለአስመጪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶችን በዕዝል 7 ስር በተገለፀበት መልኩ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡-

1. ለሚያስመጣው መሳሪያ ማከማቻ መጋዘን መኖር አለበት፤
2. አስፈላጊ ባለሙያ ወይም ቴክኒሽያን ማሟላት አለበት፤
3. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ እና የእሳት አደጋ መከላከያ በመጋዘን ውስጥ መኖር አለበት፡፡

# ክፍል አራት

# ስለ ግብርና ሜካናይዜሽን ባለሙያና ቴክኒሽያን

## 17) የባለሙያና ቴክኒሽያን ብዛትና ስብጥር

1. የግብርና መሳሪያ አምራች ወይም ገጣጣሚ ድርጅት ቢያንስ የሚከተሉትን የባለሙያ ወይም የቴክኒሽያን ስብጥር ማሟላት አለበት፡-
   ሀ. ከፍተኛ የግብርና መሳሪያ አምራች ወይም ገጣጣሚ ሰው ቢያንስ አንድ የወርክሾፕ ኃላፊ፣ አንድ ሱፐርቫይዘር፣ አንድ የምርት ክትትል ኃላፊ፤ አንድ የጥራት ተቆጣጣሪ፣ ሁለት የግብይትና ሽያጭ፣ አንድ የግዥና አቅርቦት እንዲሁም አንድ የዲዛይንና ደቨሎፐመንት ባለሙያዎች፣ አንድ የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ እና አስፈላጊ አምራች ባለሙያዎችና ቴክኒሽያኖችን ማሟላት አለበት፤
   ለ. መካከለኛ የግብርና መሳሪያ አምራች ድርጅት ቢያንስ አንድ የወርክሾፐና የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ፣ አንድ ሱፐርቫይዘር፣ አንድ የግብይትና ሽያጭ፣ አንድ የጥራት ቁጥጥር፣ አንድ የግዥና አቅርቦት፣ አንድ የምርት ክትትል ኃላፊ፣ አንድ የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ እና አስፈላጊ አምራች ባለሙያዎችና ቴክኒሽያኖችን ማሟላት አለበት፤
   ሐ. አነስተኛ የግብርና መሳሪያዎች አምራች ድርጅት ቢያንስ አንድ ወርክሾፐና የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ እና አንድ የሽያጭ ባለሙያና ቴክኒሽያን ማሟላት አለበት፡፡
2. የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት ቢያንስ የሚከተሉትን የባለሙያ ወይም ቴክኒሽያን ቁጥር ማሟላት አለበት፡-
   ሀ. ከፍተኛ የግብርና መሳሪያዎች አስመጪ ድርጅት ቢያንስ አንድ የወርክሾፕ ኃላፊ፣ አንድ የግብይትና ሽያጭ፣ አንድ የግዥና አቅርቦት፣ የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ እና አስፈላጊ ባለሙያዎችን ማሟላት አለበት፤
   ለ. መካከለኛ የግብርና መሳሪያዎች አስመጪ ድርጅት ቢያንስ አንድ የወርክሾፐና የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ፣ አንድ የግዥና አቅርቦት፣ አንድ የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ባለሙያና ቴክኒሽያን ማሟላት አለበት፤

ሐ. አነስተኛ የግብርና መሳሪያዎች አስመጪ ድርጅት ቢያንስ አንድ የግብይትና ሽያጭ ባለሙያ ማሟላት አለበት፡፡

## 18) የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እስከ 16 የተዘረዘሩት ባለሙያና ቴክኒሽያን በግብርና መሳሪያ አምራች፣ ገጣጣሚ፣ አስመጪ ወይም ላኪ ድርጅት ውስጥ ለመስራት የሚከተሉትን የትምህርት ዝግጅትና አግባብ ያለው የሥራ ልምድ በማሟላት የድርጅቱ ተቀጣሪ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የተሟላ ዝርዝር መረጃ፣ የቅጥር ውልና የቅጥር ደብዳቤ ሊኖራቸው ይገባል፤
2) በከፍተኛ የግብርና መሳሪያዎች አምራች ድርጅቶች ባለሙያ ወይም ቴክኒሽያን ሆኖ ለመስራት አስፈላጊ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ፡-

ሀ.የወርክሾፕ ኃላፊ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣ በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አምስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ለ. ሱፐር ቫይዘር ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አራት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ሐ.የግብይትና ሽያጭ ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ 4 ዓመት አግባብ ያለው የስራ ልምድ ያለው፤

መ.የጥራት ቁጥጥር ማረጋገጫ ኃላፊ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አራት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ሠ.የምርት ክትትል ኃላፊ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣ በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አራት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ረ.አምራች ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ሰ.የዲዛይንና ደቨሎፕመንት ከፍተኛ ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣ በመካኒካል ዲዛይን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አራት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ሸ.የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው፡፡

3. በመካከለኛ የግብርና መሳሪያዎች አምራች ድርጅቶች ባለሙያ ወይም ቴክኒሽያን ሆኖ ለመስራት አስፈላጊ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ መስፈርት፤

ሀ.የወርክሾፕ ኃላፊ ሆኖ ለመስራት ለመሆን በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣ በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሶስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ለ.ሱፐር ቫይዘር ሆኖ ለመስራት ለመሆን በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሶስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ሐ.የግብይትና ሽያጭ ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አንድ ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

መ.የጥራት ቁጥጥር ማረጋገጫ ኃላፊ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ሠ.የምርት ክትትል ኃላፊ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ረ.አምራች ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አንድ ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ሰ.የዲዛይንና ደቨሎፐመንት ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣ በመካኒካል ዲዛይን ምህንድስ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ሸ.የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አንድ ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት።

4. በአነስተኛ የግብርና መሳሪያዎች አምራች ድርጅቶች ባለሙያ ወይም ቴክኒሽያን ሆኖ ለመስራት አስፈላጊ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ መስፈርት፤

ሀ.የወርክሾፕና የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ ሆኖ ለመስራት ለመሆን በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣ በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሶስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤

ለ.የግብይትና ሽያጭ ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አንድ ዓመት የስራ

ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፡፡

5. በከፍተኛ የግብርና መሳሪያዎች አስመጪ ድርጅቶች ባለሙያ ወይም ቴክኒሽያን ሆኖ ለመስራት አስፈላጊ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ መስፈርት፤
   ሀ.የወርክሾፕ ኃላፊ ሆኖ ለመስራት ለመሆን በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አምስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤
   ለ. የግብይትና ሽያጭ ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ አራት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤
   ሐ.የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ አራት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፡፡

6. በመካከለኛ  የግብርና መሳሪያዎች አስመጪ ድርጅቶች ባለሙያ ወይም ቴክኒሽያን ሆኖ ለመስራት አስፈላጊ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ መስፈርት፤
   ሀ. የወርክሾፕና የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ኃላፊ ሆኖ ለመስራት ለመሆን በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና፣ በመካኒካል ምህንድስና፣ በማንፋክቸሪንግ ምህንድስና፣ በአውቶሞቲቭ ኢንጅነሪንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አራት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፤
   ለ. የሽያጭ መሐንዲስ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም በግብርና ባዮፕሮሰሲንግ ከዚህ ጋር ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ አንድ ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፡፡
7. በአነስተኛ የግብርና መሳሪያዎች አስመጪ ድርጅቶች የግብይትና ሽያጭ ባለሙያ ሆኖ ለመስራት በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና መካናይዜሽን ምህንድስና ወይም ተዛማጅ የትምህርት ዘርፎች በዲግሪ የተመረቀና ቢያንስ ዜሮ ዓመት የስራ ልምድ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በደረጃ 4 የተመረቀና ቢያንስ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡

# ክፍል አምስት
# ስለግብርና መሳሪያ ገላጭ ጽሁፍ

## 19) የግብርና መሳሪያ ገላጭ ጽሁፍ ይዘት

1. ማንኛውም ሰው ለሚያመርተው፣ ለሚገጣጥመው፣ ለሚያስመጣው ወይም ለሚልከው የግብርና መሳሪያ ገላጭ ፅሁፍ በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል፤

2. ማንኛውም የግብርና መሳሪያ ገላጭ ጽሁፍ ግልፅ፣ በቀላሉ የሚነበብና የማይለቅ ሆኖ ቢያንስ የሚከተለትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፡-
   ሀ) የመሳሪያው ስም፣
   ለ) የመሳሪያው ሞዴል፣ ሞተር ቁጥር፤ መለያ ቁጥር ወይም ቻንሲ ቁጥር፣
   ሐ) የአምራቹ ወይም ገጣጣሚው ድርጅት ስም ከነሙሉ አድራሻ፣
   መ) መሳሪያው የተመረተበት ጊዜ፤
   ሠ) ያገለገለ መሳሪያ ከሆነ ከተህዋስያን ነፃ ስለመሆኑ ‹‹ከተህዋስያን ነፃ›› የሚል ጽሁፍ፤
3. በመሳሪያው ላይ ገላጭ ፅሑፍ ለማተም የማይመች እና የማይበቃ ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተቀመጡትን መረጃዎች እንደአስፈላጊነቱ በማሸጊያው ላይ ወይም በተጨማሪ በራሪ ወረቀት መገለጽ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ስድስት
# ስለግብርና መሳሪያ ድህረ-ሽያጭ አገልግሎቶች

## 20) ስለድህረ-ሽያጭ አገልግሎት አይነቶችና መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች

አስመጪ ወይም አምራች ወይም ገጣጣሚ ሰው ለሚያስመጣቸው መሳሪያ የሚከተሉትን የድህረ-ሽያጭ አገልግሎቶች መስጠት አለበት፡-

1. በግብርና መሳሪያ ሽያጭ ወቅት ተገቢውን የኦፐሬቲንግ ማኑዋል፣ የመለዋወጫ ማኑዋል እና ተመሳሳይ ሰነዶችን አሟልቶ ለተገልጋይ መስጠት አለበት፤
2. ወደ ሀገር ውስጥ ለገባው ወይም በሀገር ውስጥ ለተመረተው ወይም ለተገጣጠመው የግብርና መሳሪያ የአጠቃቀምና የጥንቃቄ ስልጠና ለሚመለከተው አካል መስጠት አለበት፤
3. ወደ ሀገር ውስጥ ለገባው ወይም በሀገር ውስጥ ለተመረተው ወይም ለተገጣጠመው የግብርና መሳሪያ በመስክ ስራ ላይ የሚያጋጥም የቴክኒክ ችግር መኖሩንና አለመኖሩን የሚያረጋግጥበት አሰራር መዘርጋት አለበት፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በመሳሪያው ላይ የተገኘ ችግር ተለይቶ ከታወቀ ምክንያቱንና መፍትሄውን አካቶ ለሚመለከተው አካል ስልጠና መስጠት ይኖርበታል፤
5. ተጠቃሚው በሚፈልገው ቦታ የጥገና አገልግሎት መስጠት አለበት፤
6. ስለተሰጠው የሥራ ላይ ስልጠና፣ የሽያጭ፣ የጥገና እና የመለዋወጫ ሁኔታ ለባለስልጣኑ በሚዘጋጅ ቅጽ መሰረት በየስድስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል፤
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በመሳሪያው ላይ የተገኘው ችግር ተለይቶ ከታወቀ እና ተደጋጋሚ ከሆነ አቅራቢው የመሳሪያው ችግር የሚቀርፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል፤
8. የመለዋወጫ ፍላጎት ጥናት በማካሄድ በቂ አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፤
9. አዲስ በሚቀርቡ ሞዴሎች ላይ ወቅታዊ ስልጠና ያዘጋጃል፤
10. በዋስትና ጊዜ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮች የሚፈቱበትና ወቅታዊ የጥገና አገልግሎት እና ለቅያሪ የሚስፈልግ መለዋወጫ የሚቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
11. ተጠቃሚው የጥገና አገልግሎት በጠየቀ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል፤

12. የድህረ ሽያጭ አገልግሎት በተጠቃሚው አማካይ በሆነ አካባቢ የጥገናና የመለዋወጫ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል

# ክፍል ሰባት

## ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት እና ወደ ውጭ ስለመላክ

### 21) የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት

1. ማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግበትን የግብርና መሳሪያ አስመጪ ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት አይችልም፤
2. ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ የግብርና መሳሪያ የግብርና ስታንዳርድ ወይም አለም አቀፍ ተቀባይነት ያላውን ደረጃ ያሟላ መሆን አለበት፤
3. ማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግበት የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ሕጋዊ የግብርና መሳሪያ ማስገቢያ ፈቃድ በተሰጠው የግብርና መሳሪያ አስመጪ ድርጅት ብቻ ነው፤
4. ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ አዲስ የግብርና መሳሪያ በባለስልጣኑ የተመዘገበ መሆን አለበት፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የተጠቀሰው ቢኖርም አስገዳጅና አሳማኝ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጥራትና ደህንነት መስፈርቶችን በማረጋገጥ የግብርና መሳሪያ በልዩ ሁኔታ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ባለስልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፤
6. አስመጪው የሚያስመጣው የግብርና መሳሪያ ከሀገሪቱ የአየር ፀባይና የመልክዓ ምድር አቀማመጥ እንዲሁም ከብክለት የፀዳ መሆን አለበት፤
7. ማንኛውም የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው መስፈርቱን በሚያሟላ መግቢያ በሮች ብቻ መሆን አለበት፤
8. የግብርና መሳሪያው ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በምዝገባ/በቅድመ ማስገቢያ ወቅት ከቀረበው መረጃ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ሊኖረው ይገባል፤
9. ማንኛውም ሰው ከሚያስመጣው የግብርና መሳሪያ ጋር አብረው የሚመጡ መረጃዎችና ገላጭ ፅሁፎች በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ወይም በሁለቱም ቋንቋዎች የተፃፉ መሆን አለባቸው፡፡

### 22) በልዩ ሁኔታ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገባ የግብርና መሳሪያ

ባለስልጣኑ በሚከተሉት ሁኔታዎች ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፤ የምዝገባ ፈቃድ እና የግዥ ትዕዛዝ ሳያስፈልግ እና ሌሎች መስፈርቶችን እንደአስፈላጊነታቸዉ በማሟላት የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የሚያስችል ልዩ የመልቀቂያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

1. ለሳይንሳዊ ምርምር እና ለትምህርት ተቋማት ለማስተማሪያ አገልግሎት የሚውል መሳሪያ ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ፤
2. ለአጭር ጊዜ ትምህርት፣ ስልጠና ወይም አውደ ርዕይ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ሲፈለግ፤
3. ለአስቸኳይ አደጋ፣ ለሰብልና እንስሳት ሕይወት አድን ተግባር ሲባል ወደ ሀገር ውስጥ መሳሪያ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ፤
4. በእርዳታ የመጣ ከሆነ፤
5. ለራስ ፍጆታ የሚውል መሳሪያ ከሆነ፤
6. ከላይ በዚህ አንቀጽ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተፈጠረው አጋጣሚ፣ ችግር ወይም ሁኔታ በማሳበብ የሚከናወን ሕገ-ወጥ ተግባር በማስረጃ ሲረጋገጥ በሕግ አግባብ አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

## 23) የግብርና መሳሪያ ወደ ውጭ ስለመላክ

1. ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የመውጫ ፈቃድ ሳያገኝ የግብርና መሳሪያ ወደ ውጭ ሀገር መላክ አይችልም፤
2. ማንኛውም ወደ ውጭ ሀገር የሚወጣ መሳሪያ በባለሥልጣኑ የተመዘገበ መሆን አለበት፤
3. ማንኛውም ወደ ውጭ ሀገር የሚወጣ መሳሪያ ፈቃድ የሚሰጠው ሀገሪቱ ባወጣችው ወይም በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የግብርና ስታንዳርድ ወይም የተቀባዩን ሀገር ፍላጎት አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡

# ክፍል ስምንት
# ስለቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ

## 24) የቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታ

1. ማንኛውም ሰው ቁጥጥር የሚደረግበትን የግብርና መሳሪያ ከማስመጣቱ በፊት የቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ ከባለስልጣኑ ማግኘት አለበት፤
2. በባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ለግብርና መሳሪያ የተሰጠ የቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ብቻ መስፈርቱን አሟልቶ ሀገር ውስጥ መግባት አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጹት እንደተጠበቁ ሆነው በማስገቢያ ፈቃዱ በጊዜ ገደብ መሠረት መሳሪያው ሀገር ውስጥ ወይም የጉምሩክ አሰራር ሂደት ውስጥ ሳይገባ የተሰጠው የ6ወር የፈቃድ ጊዜ ካለፈ የማስገቢያ ፈቃዱን ማደስ ይጠበቅበታል፡፡

## 25) የቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች

ማንኛውም አስመጪ ሰው እንደመሳሪያው አይነት የቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልቶ በአካል ወይም በኢ-ሰርቪስ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡-

1. አዲስ ባለሞተርና የሚንቀሳቀስ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስመጣት የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፤
   ሀ. አስመጪው ከአምራች ኩባንያው ውክልና ያለው ከሆነ የሰነዱ ቅጂ፣
   ለ. የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣
   ሐ. ከባለስልጣኑ የተሰጠ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣
   መ. መሳሪያው ከተመረተ ከሁለት ዓመት ያልበለጠው መሆን አለበት፣
   ሠ. መሳሪያው እና የመሳሪያው ሞተር በላኪው ሀገር የተመዘገበበት ማረጋገጫ፣
   ረ. መሳሪያው የጥራት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት (የአይ ኤስ ኦ ወይም አቻ) ሊኖረው ይገባል፣
   ሰ. የብቃት ማረጋገጫ ባለው ድርጅት የተመረተ ስለመሆኑ ማረጋገጫ፣
   ሸ. የመሳሪያው ዝርዝር መስፈርቶች፣
   ቀ. የዋጋ ማቅረቢያ እና ከሚያስመጣው ጠቅላላ የመሳሪያ ዋጋ ቢያንስ 15 በመቶ የመለዋወጫ ዕቃ ስለማስገባቱ የመለዋወጫ ዕቃ ግዥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

2. ያገለገለ ባለሞተርና የሚንቀሳቀስ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስመጣት የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-
   ሀ. የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ
   ለ. ከባለስልጣኑ የተሰጠ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣
   ሐ. መሳሪያው ከተመረተና አገልግሎት ከሰጠ ከአምስት ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት
   መ. ከአፈር፣ ከዕፅዋት ዘር፣ ከኳራንቲን ተባይ፣ከእንስሳት በሽታ ወይንም ከዕፅዋት እና ከእንስሳት ተረፈ ምርት ነፃ መሆኑን የማንጽያ ማስረጃ፣ የሕክምና የምስክር ወረቀት፣የዕፅዋት ወይም የእንስሳት ጤንነት ማረጋገጫ የፋይቶ ሳኒተሪ የምስክር ወረቀት ከመጣበት ሀገር ሊኖረው ይገባል፣
   ሠ. የመሳሪያው ዝርዝር መስፈርቶች
   ረ. የዋጋ ማቅረቢያ፣ የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ ቢያንስ 10 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ
   ሰ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ረ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበ ሰው የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ 10 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት፤ ነገርግን የሚመጣው መሳሪያ በሀገር ውስጥ ሕጋዊ ወኪል ያለው ከሆነ የመለዋወጫ ዕቃ እንዲያመጣ አይገደድም፡፡

3. አዲስ ባለሞተርና የማይንቀሳቀስ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስመጣት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-
   ሀ. መሳሪያው ከተመረተ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፤
   ለ. አስመጪው ከአምራች ኩባንያው ውክልና ያለው መሆን፤
   ሐ. የመሳሪያው እና የመሳሪያው ሞተር በላኪው ሀገር የተመዘገቡና የብቃት ማረጋገጫ ባለው ድርጅት የተመረተ ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤
   መ. የጥራት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት (የአይ ኤስ ኦ ወይም አቻ ሰርቲፊኬት)፤
   ሠ. የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፤
   ረ. ከባለስልጣኑ የተሰጠ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣
   ሰ. የመሳሪያው ዝርዝር መስፈርቶች፤
   ሸ. የዋጋ ማቅረቢያ፣ የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ ቢያንስ 5 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ፤

ቀ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሸ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበ ሰው የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ 5 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት አለበት፤ነገርግን የሚመጣው መሳሪያ በሀገር ውስጥ ሕጋዊ ወኪል ያለው ከሆነ የመለዋወጫ ዕቃ እንዲያመጣ አይገደድም፡፡

4. አዲስ እስከ 12 የፈረስ ጉልበት ባለው ሞተር፣ በሰው ወይም በእንስሳት ጉልበት የሚሰሩ ሆነው የማይንቀሳቀሱ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስመጣት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ. የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፤
ለ. ከባለስልጣኑ የተሰጠ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣
ሐ. የመሳሪያው ዝርዝር መስፈርቶች (እንደ መሳሪያው አይነት የሚወሰን)፣
መ. የዋጋ ማቅረቢያ፣ የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ ቢያንስ 2 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ፤
ሠ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ መ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበ ሰው የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ 2 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት አለበት.ነገርግን የሚመጣው መሳሪያ በሀገር ውስጥ ሕጋዊ ወኪል ያለው ከሆነ የመለዋወጫ ዕቃ እንዲያመጣ አይገደድም፡፡

5. አዲስ የማሽን ተቀጽላ መሳሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስመጣት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፤
ሀ. አስመጪው ከአምራች ኩባንያው ውክልና ስለመኖር፤
ለ. መሳሪያው በላኪው ሀገር የተመዘገበና የብቃት ማረጋገጫ ባለው ድርጅት የተመረተ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ (የአይ ኤስ ኦ ወይም አቻ)፤
ሐ. የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፤
መ. ከባለስልጣኑ የተሰጠ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣
ሠ. የመሳሪያው ዝርዝር መስፈርቶች፤
ረ. የዋጋ ማቅረቢያ፣ የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ ቢያንስ 3 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ፤
ሰ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ረ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበ ሰው የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ 3 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት አለበት፣ነገርግን የሚመጣው መሳሪያ በሀገር ውስጥ ሕጋዊ ወኪል ያለው ከሆነ የመለዋወጫ ዕቃ እንዲያመጣ አይገደድም፡፡

6. በልዩ ሁኔታ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ጥያቄ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 እና በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የተገለጸው እንደአግባቡ የተጠበቀ ሆኖ ጥያቄ አቅራቢው ሰው ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ማስረጃዎችን ማቅረብ አለበት፤
ሀ. ለሳይንሳዊ ምርምር እና ለትምህርት ተቋማት ለማስተማሪያ አገልግሎት የሚውል መሳሪያ ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ የምርምር ተቋማት ወይም የዩኒቨርሲቲ የማረጋገጫ ደብዳቤ እንዲሁም መሳሪያው የተመረተበት ሀገርና ተያያዥ መረጃዎች ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

ለ. ለአጭር ጊዜ ትምህርት፣ ስልጠና ወይም አውደ ርዕይ በልዩ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ሲፈለግ ስልጠናው ወይም አውደርዕዩ ከሚያስተባብረው አካል የድጋፍ ደብዳቤ፣ የሚካሄድበት ጊዜ፤ መሳሪያው የተመረተበት ሀገርና ተያያዥ መረጃዎች ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

ሐ. ለአስቸኳይ አደጋ፣ ለሰብልና እንስሳት ሕይወት አድን ተግባር ሲባል ወደ ሀገር ውስጥ መሳሪያ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርብ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም በአካባቢው ስለተከሰተው አደጋ የሚገልጽ ደብዳቤ፣ መሳሪያው የተመረተበት ሀገርና ተያያዥ መረጃዎች ተያያዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

መ. በእርዳታ የመጣ ከሆነ የእርዳታ ለመሆኑ ከረጂው ድርጅት የተሰጠ ማረጋገጫ ወረቀት፣

ሠ. ለራስ ፍጆታ የሚውል መሳሪያ ከሆነ ጠያቂው ሰው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የአምራችነት ፈቃድ መኖሩን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው መሳሪያ ለራስ ፍጆታ እንደሚውል የጽሁፍ ማረጋገጫ፣ መሳሪያው የተመረተበት ሀገርና ተያያዥ መረጃዎች ተያያዞ መቅረብ ይኖርበታል።

7. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ጥያቄ ሲቀርብ ከዚህ በታች በተገለፀበት መልኩ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት አለበት፡-

ሀ. ያገለገለ ባለሞተርና የሚንቀሳቀስ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር በልዩ ሁኔታ ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበ ሰው የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ 10 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት አለበት፤

ለ. አዲስ ባለሞተርና የማይንቀሳቀስ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ በልዩ ሁኔታ ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበ ሰው የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ 5 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት አለበት፤

ሐ. አዲስ እስከ 12 የፈረስ ጉልበት ባለው ሞተር፣ በሰው ወይም በእንስሳት ጉልበት የሚሰሩ ሆነው የማይንቀሳቀሱ የግብርና መሳሪያ ወደ ሀገር ውስጥ በልዩ ሁኔታ ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበ ሰው የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ 2 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት አለበት፤

መ. አዲስ የማሽን ተቀጽላ መሳሪያዎች ወደ ሀገር ውስጥ በልዩ ሁኔታ ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበ ሰው የሚያስመጣውን መሳሪያ ዋጋ 3 በመቶ ያላነሰ የመለዋወጫ ዕቃ ማስመጣት አለበት፤

ሠ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ሀገር ውስጥ የሚመጣው መሳሪያ በሀገር ውስጥ ሕጋዊ ወኪል ያለው ከሆነ የመለዋወጫ ዕቃ እንዲያመጣ አይገደድም።

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአውደ ርዕይ በልዩ ሁኔታ ለማስገባት የተፈቀደለት ሰው የመሳሪያውን መለዋወጫ እንዲያቀርብ አይገደድም፤

9. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 6 እስከ 8 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተፈጠረው አጋጣሚ፣ ችግር ወይም ሁኔታ በማሳበብ የሚከናወን ሕገ-ወጥ ተግባር በማስረጃ ሲረጋገጥ በሕግ አግባብ አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል።

## ክፍል ዘጠኝ
## ከጉምሩክ በር መልቀቂያ ፈቃድ ስለመስጠት

## 26) ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ የግብርና መሳሪያ ከጉምሩክ በር የመልቀቂያ ፈቃድ ስለመስጠት

1. ማንኛውም ሰው ቁጥጥር የሚደረግበትን የግብርና መሳሪያ ከመውጫና መግቢያ ኬላ ላይ በማስለቀቅ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው (ዕዝል 1) ጋር አያይዞ በአካል ወይም በአንድ መስኮት አገልግሎት ማቅረብ አለበት፤
   ሀ. የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ፣
   ለ. የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣
   ሐ. ከባለስልጣኑ የተሰጠ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣
   መ. የጉምሩክ ዲክሊራሲዮን (የትራንዚት ፈቃድ ያገኘበት ማህተም ያለው)፣
   ሠ. ኦርጂናል የግዥ ትዕዛዝ ፈቃድ፣
   ረ. የመሳሪያው ስሪት ሀገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ቻምበራይዝድ የሆነ፣
   ሰ. የዓለም አቀፍ የፍተሻና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከነፍተሻ ሰነዱ፣
   ሸ. የጥቅል ጭነት ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፣
   ቀ. የመንገድ የምስክር ወረቀት (ምርቱ ከተነሳበት ቀን ጀምሮ የመጨረሻው ፍተሻ ጣቢያ እስኪደርስ ድረስ በየቁጥጥር ጣቢያው የጉምሩክ ማህተም ያረፈበት የምስክር ወረቀት) በየብስ ለሚገቡና የተለያዩ ጣቢያዎችን የሚያልፍ ከሆነ፣
   በ. የአየር ወይም የየብስ ማጓጓዣ ሰነድ፤
   ተ. የግዥ ደረሰኝ፤
   ቸ. በልዩ ሁኔታ የመጣ ከሆነ በአንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰውን ማሟላት፣
   ነ. ያገለገለ የግብርና መሳሪያ ከሆነ ከአፈር፣ ከዕፅዋት ዘር፣ ከኳራንቲን ተባይ፣ ከእንስሳት በሽታ ወይንም ከዕፅዋት እና ከእንስሳት ተረፈ ምርት ነፃ ስለመደረጉ በባለስልጣኑ ከሚመለከተው የስራ ክፍል ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

2. አንድ አስመጪ ድርጅት በግዥ ትእዛዙ ሰነድ ላይ ከተገለፀው የመሳሪያ አምራች ድርጅት ውጪ ከሌላ አምራች ድርጅት ምንም አይነት መሳሪያ ማስመጣት አይችልም፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ከተዘረዘሩት መረጃዎች ውስጥ ያልተሟሉ ወይም ትክክል ያልሆነ ሰነድ ከተገኘ ለአመልካቹ በጽሁፍ የማሳወቂያ ቅጽ (ዕዝል 8) መሠረት ማሟላት ያለበትን መረጃ በ10 ቀናት ውስጥ አሟልቶ እንዲያቀርብ ይገለጽለታል፣
4. ባለስልጣኑ ወደ ሀገር ውስጥ ከገባው መሳሪያ ብዛት ከእያንዳንዱ መሳሪያ አይነት ናሙና በማየት (ዕዝል 9) የፊዚካል ምርመራ ማድረግ ይችላል፡፡

## 27) ወደ ውጪ ሀገር ለሚወጣ የግብርና መሳሪያ የጉምሩክ የይለቀቅ ፈቃድ ስለመስጠት

1. ወደ ውጭ ሀገር የግብርና መሳሪያዎችን የሚልኩ ሕጋዊ ድርጅቶች በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ቅጽ (ዕዝል 15) በመሙላት ማመልከት አለባቸው፡፡
2. ከሀገር ውጪ የግብርና መሳሪያዎችን ለመላክ የመውጫ ፈቃድ የሚፈልጉ ድርጅቶች የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፦
   ሀ. የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ፤
   ለ. የዋጋ ማቅረቢያ ደረሰኝ፤
   ሐ. ከገዢው አካል የቀረበ የግዥ ትዕዛዝ ወይም የስምምነት ውል፤
   መ. ሽያጭ የተፈፀመበት ኢንቮይስ፤

ሠ. የሀገሪቷ ምርት ስለመሆኑ የሚያሳይ የምስክር ወረቀት፤

ረ. የጭነት ዝርዝር፤

ሰ. በእርዳታ የሚላክ ከሆነ የእርዳታ ምስክር ወረቀት፤

ሸ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፤

ቀ. የባንክ ፈቃድ።

3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 የተዘረዘሩት ሰነዶች ያልተሟሉ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ሰነድ ሆኖ ከተገኘ ለአመልካቹ በማሳወቂያ ቅጽ (ዕዝል 8) መሠረት ማሟላት ያለበትን መረጃ በ10 ቀናት ውስጥ አሟልቶ እንዲያቀርብ በፅሁፍ ይገለጽለታል፤
4. ሁሉም አስፈላጊ ሰነዶችና መረጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ባለስልጣኑ የመልቀቂያ ፈቃድ ቅጽ (ዕዝል 16) ተሞልቶ ለአመልካች ድርጅቱ በሁለት ቀን ይሰጣል፤
5. የመውጫ ፈቃድን ለሌላ ድርጅት አሳልፎ መስጠት አይቻልም፤ አገልግሎቱም ለአንድ ጭነት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል።

### 28)የግብርና መሳሪያ ከጉምሩክ በር ወደ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ ስለሚከለከልበት ሁኔታ

1. በሚከተሉት ምክንያቶች በመግቢያ ኬላ ወይም የጉምሩክ በር ወደ ሀገር ውስጥ መግባት እንደማይችል ሊወሰን ይችላል:-

   ሀ. የመጣው መሳሪያ አስፈላጊውን የመግቢያ ሰነድ እንዲያሟላ ተገልጾለት በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳያሟላ ሲቀር፤

   ለ. በቅድመ-ማስገቢያ ፈቃድ ከተጠየቀው የመሳሪያ እና የመለዋወጫ ዕቃና ዝርዝር ሁኔታ የተለየ ከሆነ፣

   ሐ. በተደረገው የፊዚካል ኢንስፔክሽን ወይም ፍተሻ የጥራት ጉድለት ከታየበት፣

   መ. በሕገ-ወጥ ሁኔታ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ከሆነ፣

   ሠ. ለሰው ወይም ለእንስሳት ጤና ወይም ለአካባቢ ብክለት ምክንያት ሆኖ ሲገኝ።
2. ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መሳሪያው እንዳይለቀቅ ሲወሰን ማቆያ ቅጽ (ዕዝል 14) በመሙላትና ምክንያቱን በግልጽ በማስቀመጥ አስመጪው እንዲያውቀው ይደረጋል።
3. መሳሪያው እንዳይለቀቅ ሲወሰን ተያያዥ ሰነዶች ላይ "የማይለቀቅ" የሚል ማህተም ይደረግባቸዋል።
4. እንዳይለቀቅ ውሳኔ የተሰጠበት መሳሪያ በባለንብረቱ ወጪ ተመልሶ ወደመጣበት ሀገር እንዲላክ ወይም እንዲወገድ ይደረጋል።

## ክፍል አስር

## ስለ ኢንስፔክተሮች

### 29)የኢንስፔክተሮች ሥልጣንና ተግባር

1) ባለስልጣኑ የባለስልጣኑን ደንብ እና ይህ መመሪያ መከበራቸውን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተመደበ ኢንስፔክተር ከንዑስ አንቀጽ 3-10 የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

3) የግብርና መሳሪያ በሚመረትበት፣ በሚገጣጠምበት የሥራ ቦታ ወይም በአስመጪው እና ላኪው የሥራ ቦታ በሥራ ሰዓት በመግባት የቁጥጥር ተግባር የማከናወን፤
4) የግብርና መሳሪያን የጫነ ተሽከርካሪን በማስቆም የቁጥጥር ተግባር የማከናወን፤
5) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ የግብርና መሳሪያን የጥራት ምርመራ የማድረግ፤
6) በሀገር ውስጥ የሚመረት ወይም የሚገጣጠም የግብርና መሳሪያን የጥራት ምርመራ የማድረግ፤
7) የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ በተጠረጠረ የግብርና መሣሪያ ላይ የደህንነት ምርመራ እንዲካሄድ የማድረግ፤
8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት የግብርና መሣሪያ የደህንነት ምርመራ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ተለይቶ እንዲቆይ የማድረግ፤
9) ከግብርና መሳሪያ ማምረት፣ መገጣጠም፣ ማስመጣትና መላክ ጋር የተዛመደ ማንኛውንም መዛግብት እና ሰነዶችን መመልከትና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ኮፒ ተደርጎ እንዲሰጠው የማድረግ፤
10) የግብርና መሳሪያ አምራች፣ ገጣጣሚ፣ አስመጪና ላኪ ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ባቀረበው የስራ መሣሪያ፣ ባለሙያና ሌሎች በመስፈርቱ ላይ የተገለጹ ሁኔታዎችን አሟልቶ እየሰራ መሆኑን የማረጋገጥ፤
11) በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምሰክር ወረቅት ሳይኖረው የግብርና መሳሪያን በሚያመርት፣ በሚገጣጥም፣ በሚስመጣና በሚልክ ሰው ላይ ቁጥጥር የማድረግ፤
12) ኢንስፔክተሩ በጉሙሩክ በር ላይ የደረሰ የግብርና መሳሪያ አስፈላጊ መስፈርቶችን መሟላቱን በማረጋገጥ የስራ ኃላፊነት እና የባለስልጣኑ ማህተም የተመታበት የመልቀቂያ ፈቃድ ይሰጣል (ዕዝል 11)፤
13) አሳማኝ የላብራቶሪ ምርመራ እንዲደረግ ከተወሰነ የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት እስኪረጋገጥ ድረስ አስመጪውን ሰው የግዴታ ውዴታ ውል በማስገባት ምርቱን ለንግድ ሳያውል በተዘጋጀ እና በተረጋገጠ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ እንዲያከማች የማድረግ፤
14) በዚህ አንቀጽ፤ንኡስ አንቀጽ 13 የተገለጸው የግብርና መሳሪያ የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት ከታወቀና ችግሩ ካልተገኘበት የመልቀቂያ ፍቃድ ይሰጣል፤
15) የሚመደቡ ኢንስፔክተሮች የባለስልጣኑን መታወቂያ ወይም ደብዳቤ ቁጥጥሩ ለሚካሄድበት ሰው ባለቤት ወይም ለህጋዊ ወኪሉ ማሳየት አለበት፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## አስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ

### 30) ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት

1. ማንኛውም የግብርና መሳሪያዎች አምራች፣ አስመጪና ላኪ ድርጅት የፈፀመው ጥፋት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚያሳግድ ወይም የሚያሰርዝ ካልሆነ በስተቀር ባለስልጣኑ እንደአግባብነቱ የቃል ወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰጠው ይችላል፡፡
   ሀ. ከተጠቀሰው ቴክኒክ ባለሙያ እውቅና ውጪ የማምረት፣ የማስመጣት ወይም የመላክ አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፤

ለ. የድህረ ሽያጭ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ካልተገበረ፤

ሐ. ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው ማንኛውም የኢንስፔክሽን ስራዎች እንዳያከናውን እንቅፋት የፈጠረ እንደሆነ፤

መ. ባለስልጣኑን ሳያሳውቅ የቦታ አድራሻ ላይ ለውጥ ካደረገ፡፡

2. ባለስልጣኑ በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት አስፈላጊውን ማስተካከያ ካላደረገ፡፡

## 31) ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ

1. ማንኛውም የግብርና መሳሪያዎች አምራች፣ አስመጪና ላኪ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ ባለስልጣኑ ጉድለቶች ወይም ጥፋቶች እስኪስተካከሉ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን እስከ 1 ወር ሊያግድበት ይችላል፡፡

   ሀ. ሕጋዊና ወቅታዊ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሌለው ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር የንግድ ስራ ፈቃዱ እንዲታገድ ይደረጋል፤

   ለ. ከተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ውጪ ሲሰራ ከተገኘ፤

   ሐ ድርጅቱ ከሁለት ጊዜ በላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ጉድለቱን ያላስተካከለ ከሆነ፤

   መ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተገኘው መስፈርቱን ሳያሟላ መሆኑ ከተረጋገጠ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት ድርጅት የተጣለበት ዕገዳ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ለዕገዳ ያበቃውን ጥፋት ካረመ ወይም ካስተካከለ ነው፡፡

## 32) ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኘ የግብርና መሳሪያዎች አምራች፣ አስመጪና ላኪ ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊሰርዝበት ይችላል፡፡
2. ባለስልጣኑ አስፈላጊ እና ምክንያታዊ ነው ብሎ ያመነባቸውን ጥፋቶች በድርጅቱ ሲፈጸም ቢያንስ ለ3 ወር የሚደርስ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ሊሰርዝ ይችላል፡፡

   ሀ. በባለስልጣኑ እንዲያስተካክል የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልፈጸመ፣

   ለ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ካስተላለፈ፤

   ሐ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በወቅቱ ካልታደሰ፣

   መ. ስለ እገዳ በተመለከተው አንቀፅ ላይ የተቀመጡትን ጥፋቶች ፈፅሞ ሲገኝ ወይም በባለስልጣኑ የተጣለበትን እገዳ በመተላለፍ ስራውን ከቀጠለ፤

   ሠ. አግባብ ባለው የመንግስት አካል በስራ ላይ እንዳይቀጥል ፈቃዱን ሲሰረዝ ወይም ስራውን በራሱ ፈቃድ ሲያቋርጥ፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ድርጅት የተሰረዘ ፈቃድ ሊተካለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ለስረዛ ያበቃውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ በማረምና አዲስ

